በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ/መ/ቁ. 216200

ቀን ፡- ግንቦት 29 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች፡- ሰለሞን አረዳ

ብርሃኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ነፃነት ተገኝ

አመልካች ፡- ወ/ሮ ፍሬሕይወት ይልማ- ጠበቃ አምሀ ጌታቸው- ቀረቡ

ተጠሪ ፡- ፋና ቦሌ ሸማቾች ኃ/የተ/የሕብረት ሥራ ማሕበር- ጠበቃ ንጉሴ ጫኔ -ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጠ፡፡

ፍርድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሠጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል ነው፡፡ የክርክሩን አመጣጥ ከሥር ፍርድ ቤት የመዝገብ ግልባጭ እንደተረዳነው አመልካች በሥር ፍርድ ቤት ከሳሽ፤ ተጠሪ ተከሳሽ ነበሩ፡፡ አመልካች ሕዳር 30 ቀን 2013 ዓ/ም በተጻፈ ክስ በተጠሪ ማሕበር በምግብና መጠጥ ቁጥጥር ዋና ክፍል ኃላፊነት የሥራ መደብ ተቀጥሬ ስሰራ ከሕግ ውጭ የሥራ ውሌን በማቋረጡ በሕብረት ሥራ ማሕበራት ሕግና በተጠሪ መተዳደሪያ ደንብ መሠረት በሽምግልና ዳኞች እንዲታይ ዳኛ ለማስመረጥና ለማስመደብ ክስ አቅርቤ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 94768 ግንቦት 15 ቀን 2011 ዓ/ም በዋለው ችሎት ጉዳዩ በሽምግልና ዳኞች ሳይሆን በሥራ ክርክር ችሎት ነው የሚታይ በማለት ክሱን ውድቅ አድርጓል፡፡ ጉዳዩ በይግባኝ ሆነ በሰበር ችሎት ተቀባይነት ያላገኘ በመሆኑ የሥራ ክርክር ችሎት ክሴን ተቀብሎ ወደሥራ እንድመለስ እንዲወሰንልኝ፣ ተጠሪ ለመመለስ ፈቃደኛ ካልሆነ ካሣ፣ የሥራ ስንብት ክፍያ፣ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ፣ ክፍያ ለዘገየበት

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ቅጣት፣ የዓመት ዕረፍት ክፍያ፣ በ2006 ዓ/ም የሐምሌ ወር ደመወዝ፣ በ2006 ዓ/ም የቡና ገለባ ሽያጭ በሕብረት ሥምምነቱ መሠረት ሊከፈለኝ የሚገባ ብር 1,900.00 እንዲከፈለኝ፣ የሥራ ምስክር ወረቀት እንዲሰጠኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ አመልካች ባቀረበው የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አመልካች የሥራ መሪ በመሆናቸው ክሱ በሥራ ክርክር ችሎት ሊታይ አይገባም፣ ክሱ በይርጋ ቀሪ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡

የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የቀረቡትን መቃወሚያዎች መርምሮ አመልካች በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 2(10) የተመለከተውን የሥራ መሪ መስፈርት የማያሟሉ በመሆኑ ጉዳዩ በአሠሪና ሠራተኛ ሕግ መሠረት ለሥራ ክርክር ችሎት መቅረቡ ተገቢ ነው፡፡ አመልካች የሥራ ውላቸው ከተቋረጠ ከሁለት ዓመት በኋላ ያቀረቡት ክስ ሲሆን ቀደም ሲል በሌላ ሥልጣን በሌለው ፍርድ ቤት ክስ ማቅረባቸው ሰበር ችሎቱ በመዝገብ ቁጥር 16648 በሠጠው ትርጉም መሠረት ይርጋን የማያቋርጥ በመሆኑ በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 163(4) መሠረት ክሱ በይርጋ ቀሪ ነው በማለት ውድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በበኩሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 16648 የሰጠው ትርጉም በመለወጥ በመዝገብ ቁጥር 36730 (በቅጽ 9 እንደታተመ) ሥልጣን በሌለው ፍርድ ቤት ክስ ቀርቦ ክርክር ላይ መቆየቱ ይርጋን ለማቋረጥ በቂ ምክንያት መሆኑ ላይ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ ነገር ግን አመልካች ቀደም ሲል ያቀረቡት ክስ ግንቦት 15 ቀን 2011 ዓ/ም ውሳኔ ያገኘ በመሆኑ ሥልጣን በሌለው ፍርድ ቤት ውሳኔ ከተሰጠበት ጊዜ ጀምሮ አመልካች ክስ እስካቀረቡበት ሕዳር 30 ቀን 2013 ዓ/ም ድረስ የሦስት ወርና የስድስት ወር ጊዜ ያለፈ በመሆኑ ክሱ በይርጋ ቀሪ መደረጉ ተገቢ ነው በማለት የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔን አጽንቷል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ይዘትም አሁን ከተያዘው ጉዳይ በፊት የቀረበው ክስ ላይ በተሰጠው ውሳኔ በይግባኝ በመዝገብ ቁጥር 237627 እንዲሁም ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ድረስ ሄዶ በመዝገብ ቁጥር 192671 ሰኔ 08 ቀን 2012 ዓ/ም የመጨረሻ ውሳኔ የተሰጠበት ስለሆነ እስከ ሰኔ 08 ቀን 2012 ዓ/ም ድረስ ያለው ጊዜ ይርጋው እንደተቋረጠ መወሰድ ሲገባው የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ውሳኔ የሰጠበት ጊዜ መሠረት ተደርጎ ክሱ በይርጋ ቀሪ ነው መባሉ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው የሚል ነው፡፡ የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን ተመልክቶ የቀደመው ክስ ሰበር ሰሚ ችሎት ቀርቦ በመዝገብ ቁጥር 192671 ሰኔ 08 ቀን 2012 ዓ/ም ተወስኗል ከተባው አንጻር ክሱ በይርጋ ቀሪ ነው መባሉ ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 36730 ከሠጠው ትርጉምና ከአሠሪና ሠራተኛ ሕጉ አኳያ ሕጋዊነቱን ለመመርመር ተጠሪ መልስ እንዲያቀርብ አዟል፡፡ ተጠሪ ያቀረበው መልስ የቀድሞው ክርክር ከተወሰነ በኋላ ክስ እስከቀረበበት ጊዜ ድረስ ስድስት ወር ጊዜ አልፏል፡፡ ፍርድ ቤት ሥልጣን የለኝም ካለ ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ወዲያውኑ ማቅረብ ሲገባቸው መዘግየታቸው ቸልተኛ መሆናቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ ውሳኔው ተገቢ ስለሆነ ሊጸና ይገባል ብሏል፡፡ አመልካች የመልሰ መልስ በማቅረብ የሰበር አቤቱታቸውን አጠናክረው ተከራክረዋል፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም ተጠሪ ያቀረቡት ክስ በይርጋ የታገደ መሆን አለመሆኑን? በጭብጥነት በመያዝ መዝገቡን መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው አመልካች ክስ ያቀረቡት በተጠሪ ማሕበር ጥር 03 ቀን 2011 ዓ/ም የተደረገው የሥራ ውል ማቋረጥ ተግባር ሕገ-ወጥ በመሆኑ ወደስራ እንዲመልሰኝ ወይም የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፈሉኝ ይወሰንልኝ የሚል ሲሆን ተጠሪ የይርጋ መቃወሚያ አቅርቧል፡፡ አመልካች ክሳቸውን የመሰረቱት አሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/1996 ሲሆን የሥር ፍርድ ቤቶች ለጉዳዩ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 ተፈጻሚ አድርገዋል፡፡ አመልካች ከሥራ የተሰናበቱት የአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/1996 በሥራ ላይ ባለበት ጊዜ ጥር 03 ቀን 2011 ዓ/ም ነው፡፡ የአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 190(5) ላይ የመሸጋገሪያ ድንጋጌ ያለው ሲሆን በዳኝነት አካል ላይ በመታየት ላይ ያሉ ጉዳዮች በተጀመሩበት ጊዜ በነበረው ሕግ መሠረት ፍጻሜ እንደሚያገኙ አስቀምጧል፡፡ በመርሕ ደረጃ መሠረታዊ ሕግ ተፈጻሚ መሆን ያለበት በሥራ ላይ ከዋለበት ጊዜ ጀምሮ በተከሰቱ ጉዳዮች ላይ ነው፡፡ ለተጠሪዎች የሥራ ውል መቋረጥ ምክንያት የሆነው ድርጊት የተከሰተው አዋጅ ቁጥር 377/1996 በሥራ ላይ ባለበት ጊዜ ስለሆነ የተግባሩ ሕጋዊነትም ሆነ መብቱ ቀሪ የሚሆንበት አግባብ መመርመር ያለበት ይሕንኑ ሕግ መሠረት በማድረግ ሊሆን ይገባል፡፡ ስለሆነም ጉዳዩ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 መሠረት ሊመረመር የሚገባው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

አመልካች የጠየቁት ዳኝነት ወደሥራ መመለስ፣ ወደሥራ መመለስ የማይችሉ ከሆነ የሕገ-ወጥ ስንብት ውጤቶች የሆኑ ክፍያዎች እንዲሁም በሥራ ላይ እያሉ በ2006 ዓ/ም ያልተከፈላቸው ክፍያ እንዲከፈላቸው ነው፡፡ ለቀረበው ክስ ተጠሪ የይርጋ መቃወሚያ አቅርቧል፡፡ የይርጋ ክርክሩ የቀረበው አመልካች ክሱን ለማቅረብ የክስ የማቅረቢያ ጊዜው (limitation of action) አልፏል በሚል ነው፡፡ ይርጋ መብትን (extinctive prescription) ወይም መብትን ለማስከበር የሚቀርብ ክስን ቀሪ የሚያደርግ ነው፡፡ እንደተጠየቀው ዳኝነት ዓይነትና ባሕሪ የይርጋ ጊዜው ሆነ መብቱ የሚጠየቅበት ጊዜ የተለያየ ነው፡፡ ወደሥራ ለመመለስ የሚቀርብ ዳኝነት በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 162(2) መሠረት የሥራ ውሉ በተቋረጠ በሦስት ወር ጊዜ ውስጥ መቅረብ አለበት፡፡ የሥራ ውሉ በመቋረጡ ምክንያት የሚጠየቁ ክፍያዎች ደግሞ በአንቀጽ 163(4) መሠረት በስድስት ወር ጊዜ መቅረብ አለባቸው፡፡ ከሥራ ውል መቋረጥ ጋር ግንኙነት የሌላቸው የደመወዝ ወይም ማንኛውም ሌላ ክፍያዎች በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 162(3) መሰረት በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ ካልቀረበ ጥያቄው በይርጋ የታገደ ስለመሆኑ ተደንግጓል፡፡

የይርጋ ጊዜ መቆጠር የሚጀምረው በመብቱ ለመጠቀም ከሚቻልበት ቀን ቀጥሎ ካለው ቀን ጀምሮ ስለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 163(1) ላይ ተመልክቷል፡፡ የአመልካች የሥራ ውል የተቋረጠው ጥር 03 ቀን 2011 ዓ/ም በመሆኑ ከሥራ ውል መቋረጥ ጋር ተያያዥ የሆኑ ዳኝነቶችን ከጥር 04 ቀን 2011 ዓ/ም ጀምሮ በሦስት ወር ወይም በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ መጠየቅ አለባቸው፡፡ አመልካች ክስ ያቀረቡት ጊዜው ካለፈ በኂላ ሕዳር 30 ቀን 2013 ዓ/ም ነው፡፡ የይርጋ ጊዜው ግን በሕግ አግባብ ሊቋረጥና እንደ አዲስ መቆጠር ሊጀምር ይችላል፡፡ የአመልካች ክርክር የተመሰረተውም ይርጋው ቀደም ሲል በተደረገ ክርክር

*ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም*

ተቋርጧል በሚል ነው፡፡ በሕጉ የይርጋ ማቋረጫ ምክንያቶች የተመለከቱ በመሆኑ ከቀረበው ክርክር አኳያ ጉዳዩን መመርመር ያስፈልጋል፡፡ በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 164 ላይ ሦስት የይርጋ ጊዜ ማቋረጫ ያለ ሲሆን የሥራ ክርክርን ለሚወስን ባለስልጣን ክስ ቀርቦ ውሳኔ እስከሚሰጠበት ቀን ድረስ፣ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅን በሥራ ላይ ለማዋልና ለማስፈጸም ኃላፊነት በተሠጠው አካል አቤቱታ ቀርቦ የመጨረሻ ውሳኔ በጽሁፍ እስኪሰጥበት ቀን ድረስ እና መብቱን በጽሁፍ ሲያምንለት ወይም በከፊል ሲፈጽምለት ናቸው፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች እና ተጠሪ ቀደም ሲል ሥልጣን በሌለው ፍርድ ቤት ያደረጉት ክርክር ይርጋውን ለማቋረጥ የሚችል ስለመሆኑ የሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 36730 የሰጠውን ትርጉም መሠረት አድርጎ ወስኗል፡፡ ነገር ግን ክሱ በይርጋ ቀሪ ነው ያለው ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ተመልክቶ ሥልጣን የለኝም ያለው ፍርድ ቤት ውሳኔ ከሰጠበት ግንቦት 15 ቀን 2011 ዓ/ም ጀምሮ ክሱ እስቀረበበት ሕዳር 30 ቀን 2013 ዓ/ም ድረስ የሦስት ወር ሆነ የስድስት ወር ይርጋ ጊዜ አልፏል በማለት ነው፡፡  አመልካች በክስ አቤቱታቸው እንደገለጹትና በቀደመው ክርክር ላይ በየደረጃው ያሉ ፍርድ ቤቶች የሰጡትን ውሳኔ በማያያዝ ይርጋው ሊቋረጥ የሚገባው የመጨረሻውን ፍርድ በሰበር ችሎት ከተሰጠበት ሰኔ 08 ቀን 2012 ዓ/ም ጊዜ ጀምሮ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡ ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 36730 በሰጠው ትርጉም በዋናነት ካስቀመጣቸው ምክንያቶች መካከል የዳኝነት አካል ክስ ሲቀርብለት ሥልጣን የሌለው መሆኑን በመጀመሪያ ተመልክቶ ወደክርክሩ ሳይገባና ተከሳሽ የሆነውን ወገን ሳይጠራ ክሱን በመሰረዝ ተከራካሪዎች ጊዜ እንዳያባክኑና መብታቸው ላይ ጉዳት እንዳያደርስ መወጣት ያለበትን ኃላፊነት ባልተወጣበት ሁኔታ በክርክሩ የወሰደው ጊዜ ላይ የይርጋ ጊዜውን መቁጠር ተገቢ አይደለም፡፡ እንዲሁም የይርጋ ደንብ ከዓላማዎቹ አንዱ የማይተጋና ዳተኛ የሆነን ባለገንዘብ መቅጣት እንጂ መብቱን ለማስከበር ጥረት የሚያደርገውንና ትጋት ያለውን ከሳሽ መብቱን እንዳይጠቀም ማድረግ አይደለም የሚል ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካች ቀደም ሲል በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አሁን ክስ ያቀረቡበት ጉዳይ በአዋጅ ቁጥር 985/2009 መሠረት በሽምግልና ዳኞች እንዲታይ ባቀረቡት ክስ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 94768 ክርክር ሲያርግ ቆይቶ ግንቦት 15 ቀን 2011 ዓ/ም ውሳኔ የሰጠ ሲሆን አመልካች ይግባኝ የማቅረብ መብታቸውን በመጠቀም ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 237627 አቅርበው ፍርድ ቤቱ ግራቀኙን አከራክሮ ታህሳስ 24 ቀን 2012 ዓ/ም የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ አጽንቷል፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ በመዝገብ ቁጥር 192671 ሰኔ 08 ቀን 2012 ዓ/ም ለሰበር ችሎት አያስቀርብም ተብሎ ተሰርዟል፡፡ በመሆኑም ጉዳዩ በመጀመሪያና በይግባኝ ደረጃ በክርክር መቆየቱ እንዲሁም አመልካች መብታቸውን ለማስከበር ትጋት ሲያደረግ የነበረ መሆኑ ሲታይ ክስ የማቅረቢያ የይርጋ ጊዜው የቀደመው ክርክር ላይ የመጨረሻ ውሳኔ እስከተሰጠበት ሰኔ 08 ቀን 2012 ዓ/ም ድረስ መቋረጡን ያረጋግጣል፡፡ ስለሆነም ከሥራ ውል መቋረጥ ጋር የተያያዙ ዳኝነቶች ይርጋ ጊዜያቸው እንደ አዲስ መቆጠር የሚጀምረው ከሰኔ 09 ቀን 2012 ዓ/ም ጀምሮ ይሆናል፡፡ አመልካች ክስ ያቀረቡት ሕዳር 30 ቀን 2013 ዓ/ም ነው፡፡ አመልካች ወደሥራ ለመመለስ ዳኝነት የጠየቁ ሲሆን ዳኝነቱ በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 162(2) መሠረት

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

የሥራ ውሉ በተቋረጠ በሦስት ወር ጊዜ ውስጥ መቅረብ እንዳለበት የተመለከተ በመሆኑ ይርጋው እንደ አዲስ መቆጠር ከጀመረበት ሰኔ 09 ቀን 2012 ዓ/ም ጀምሮ ሦስት ወር ሲቆጠር ከመስከረም 09 ቀን 2013 ዓ/ም ላይ የይርጋ ጊዜው የሚያልፈበት በመሆኑ አመልካች ሕዳር 30 ቀን 2013 ዓ/ም ወደሥራ ለመመለስ ያቀረቡት ዳኝነት በይርጋ ቀሪ ሆኗል መባሉ ተገቢ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ የሥራ ውሉ በመቋረጡ ምክንያት የሚጠየቁ ክፍያዎች፤- ካሣ፣ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ፣ የሥራ ስንብት ክፍያ፣ የዓመት ዕረፍት ወደገንዘብ ተቀይሮ እንዲከፈል የቀረበው ዳኝነትና የመዘግየት ቅጣት በአዋጁ አንቀጽ 163(4) መሠረት በስድሰት ወር ጊዜ መቅረብ አለባቸው፡፡ ከሰኔ 09 ቀን 2012 ዓ/ም ጀምሮ ስድስት ወር ሲቆጠር እስከ ታህሳስ 09 ቀን 2013 ዓ/ም ድረስ ሲሆን አመልካች የይርጋ ጊዜው ሳያልፍ ሕዳር 30 ቀን 2013 ዓ/ም ክስ ያቀረቡ በመሆኑ ከሥራ ውል መቋረጥ ጋር ተያይዞ የተጠየቁ ክፍያዎች በይርጋ ቀሪ አይሆኑም፤ በዚህ ረገድ የሥር ፍርድ ቤቶች ዳኝነቱ በይርጋ ቀሪ ነው ሲሉ የደረሱበት መደምደሚያ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ የሥራ ምስክር ወረቀት ይሰጠኝ ጥያቄም በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 162(1) መሠረት በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ የሚጠየቅ በመሆኑና አመልካች ጊዜው ሳይደርስ ዳኝነት ያቀረቡ ስለሆነ ዳኝነቱ በይርጋ ሊታገድ አይገባም ብለናል፡፡

በሌላ በኩል ከሥራ ውል መቋረጥ ጋር ግንኙነት የሌላቸው የደመወዝ ወይም ማንኛውም ሌላ ክፍያዎች በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 162(3) መሰረት በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ ካልቀረበ ጥያቄው በይርጋ የታገደ ስለመሆኑ ተደንግጓል፡፡ አመልካች ከሥራ ውል መቋረጥ ጋር ያልተያያዘ በ2006 ዓ/ም የሐምሌ ወር ደመወዝ እንዲሁም በ2006 ዓ/ም የቡና ገለባ ሽያጭ በሕብረት ሥምምነቱ መሠረት ሊከፈል የሚገባ ብር 1,900.00 እንዲከፈላቸው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ ክፍያዎቹ የአመልካች የሥራ ውል ከመቋረጡ በፊት ክፍያው ከበሰለበት ጊዜ ጀምሮ ሊጠየቅ የሚችል ነው፡፡ አመልካች ክፍያው አጠቃለው መጠየቅ የነበረባቸው እስከ 2007 ዓ/ም አጋማሽ ድረስ ነው፡፡ ክፍያውን ለመጠየቅ የተመለከተው የይርጋ ጊዜ በ2007 ዓ/ም ያለፈ በመሆኑ ይርጋ ጊዜው ያለፈ ነገር ሊቋረጥና እንደ አዲስ ሊቆጥር ስለማይችል በ2011 እና በ2012 ዓ/ም ከተጠሪ ጋር ያደረጉት ክርክር የ2006 ዓ/ም ደመወዝና በሕብረት ሥምምነቱ መሠረት ከ2006 ዓ/ም እስከ 2007 ዓ/ም አጋማሽ ወራት ድረስ መጠየቂያ ጊዜው ያለፈን ክፍያ አዲስ መብት የሚሰጥ አይደለም፡፡ ስለሆነም አመልካች በ2006 ዓ/ም የሐምሌ ወር ደመወዝ እንዲሁም በ2006 ዓ/ም የቡና ገለባ ሽያጭ በሕብረት ሥምምነቱ መሠረት ሊከፈል የሚገባ ብር 1,900.00 እንዲከፈላቸው ያቀረቡት ዳኝነት በይርጋ ቀሪ ነው መባሉ ተገቢ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 274543 ነሀሴ 13 ቀን 2013 ዓ/ም እና የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 121389 ሚያዚያ 18 ቀን 2013 ዓ/ም የሠጡት ውሳኔ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡

*ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም*

2. አመልካች ወደሥራ ለመመለስ እና በ2006 ዓ/ም የሐምሌ ወር ደመወዝ እንዲሁም በ2006 ዓ/ም የቡና ገለባ ሽያጭ በሕብረት ሥምምነቱ መሠረት ሊከፈል የሚገባ ብር 1,900.00 እንዲከፈላቸው ያቀረቡት ዳኝነት በይርጋ የታገደ ነው መባሉ ተገቢ ስለሆነ ፀንቷል፡፡

3. አመልካች ካሣ፣ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ፣ የሥራ ስንብት ክፍያ፣ የዓመት ዕረፍት ወደገንዘብ ተቀይሮ እንዲከፈል የቀረበውና የመዘግየት ቅጣት እንዲሁም የምስክር ወረቀት ይሰጠኝ በሚል ያቀረቡት ዳኝነት በይርጋ የታገደ አይደለም በማለት ወስነናል፡፡

4. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የተዘጋውን መዝገብ በማንቀሰቀስ የአመልካች የሥራ ውል የተቋረጠው በሕግ አግባብ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን በማከራከርና ተገቢ ነው የሚለውን ማስረጃ በመስማት እንደየአግባብነቱ በውሳኔ ተራ ቁጥር 3 ላይ የተመለከቱ ዳኝነቶች ላይ የመሠለውን እንዲወስን ጉዳዩን በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 341(1) መሠረት መልሠናል፡፡

5. በዚህ ችሎት ለወጣ ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

<u>ትዕዛዝ</u>

- የውሳኔው ግልባጭ ለሥር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በውሳኔው መሠረት እንዲፈጽም አዘናል፡፡ ይጻፍ የስር መዝገብ ይመለስ፡፡
- መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

ማ/አ | የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ

አለበ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም